

# ቆርኔሌዎስ

- ቆርኔሌዎስ የላካቸው ሶስቱ ሰዎች ሌሊቱን በኢዮጴ አሳለፉ። በነጋታውም ጴጥሮስና ሶስቱ ሰዎች በአንድነት ወደቆርኔሌዎስ መኖሪያ ሄዱ።

- አይሁዳውያን ጓደኞቹ ምን ያስቡ ይሆን? የሙሴ ሕግ አይሁዳውያን ከአሕዛብ ጋር መጋባትም ሆነ ከእነርሱ ጋር አብሮ አማልክቶቻቸውን ማምለክ አይፈቅድም። ከዚያ ባለፈም የአይሁድ ወግ  አይሁዳዊ ከአሕዛብ ወገን የሆነን  ሰው መጎብኘትም ሆነ አብሮ መብላትና መጠጣትን አጥብቆ ይከለክላል።

- ጴጥሮስ በዚያ ስለሚሆነው ነገር ምስክሮች ይሆኑ ዘንድ ከእርሱ ጋር ስድስት አይሁዳውያንን አስከትሏል። መቼም አይሁዳውያን ወንድሞቹ ጴጥሮስ ወደአሕዛብ ቤት እንደሄደ በሚሰሙበት ጊዜ በጣም እንደሚበሳጩ እርግጠኛ ነበር።

- በቂሳርያ ቆርኔሌዎስ ቤተሰቡንና የቅርብ ወዳጆቹን ሰብስቦ የጴጥሮስን መምጣት እየተጠባበቀ ነው።

- ጴጥሮስ እንደደረሰም ቆርኔሌዎስ በጴጥሮስ እግር ስር ወድቆ ሰገደለት። ጴጥሮስ ግን እንዲነሳ ከጠየቀው በኋላ፣ “እኔም ራሴ ደግሞ እንደአንተ ሰብአዊ ፍጡር ነኝ፣” አለው። እግዚአብሔር ሰዎች ለሌሎች ሰዎችም ሆነ ለመላእክት እንዲሰግዱ አይፈልግም።
- ወደ ቤቱ ውስጠኛው ክፍል በገቡ ጊዜም በርከት ያሉ ሰዎች ተሰብስበው አገኙ። ጴጥሮስም አንድ አይሁዳዊ ከአሕዛብ ጋር እንዲተባበር የሙሴ ሕግ እንደማይፈቅፈድ ነገራቸው። አሁን መጥቶ እነኝህን አሕዛብ መጎብኘቱም እንደሕጉ ያልተፈቀደ እንደሆነ ከገለፀላቸው በኋላ እግዚአብሔር ማንንም ሰው “ያልነፃ” ብሎ እንዳይጠራ እንዳዘዘው ነገራቸው። (ጴጥሮስ በላይኛው ክፍል ሲፀልይ ሳለ ያየውን ራዕይ አስታውሱ።)

- “ለመሆኑ ወደዚህ እንድመጣ ያስላክህብኝ ለምንድነው?” በማለት ጴጥሮስ ቆርኔሌዎስን ጠየቀው። ቆርኔሌዎስም እየፀለየ ሳለ ባየው ራዕይ አንድ የሚያንፀባርቅ ልብስ ለብሶ የተገለጠለት ሰው ወደ ጴጥሮስ ሰዎችን ልኮ እንዲያስጠራው እንዳዘዘው ነገረው። ቆርኔሌዎስ በመቀጠልም፣ “እግዚአብሔር ለእኛ እንድትነግረን ያዘዘህን በሙሉ ለመስማት ተሰብሰበናል፣”አለው። ልባቸውን ከፍተው መልእክቱን ለመቀበል ዝግጁዎች ነበሩ። ጴጥሮስም ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት እንደመጣና በመካከላቸው እንዴት እንደኖረ፣ እንዴት እንደተሰቀለና እግዚአብሔርም ከሞት እንዴት እንዳስነሳው ነገራቸው። በተጨማሪም ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት ከተነሳ በኋላ ለብዙ ሰዎች ተገልጦ እንደታያቸው ነገራቸው።

- ቀጥሎም በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን ሁሉ በስሙ የኃጢአትን ይቅርታ እንደሚቀበል አረጋገጠላቸው። ከዚያም በጣም አስገራሚ ነገር ሆነ። ጴጥሮስ ገና ንግግሩን ሳይጨርስ በሚያደምጡት ሰዎች ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው። ልክ በጴንጤ ቆስጤ ቀን በሐዋርያት ላይ እንደሆነም እነኝህ ሰዎችም በሌሎች ቋንቋዎች መናገር ጀመሩ።

- ከጴጥሮስ ጋር የመጡት ስድስቱ አይሁዳውያንም በጣም ገረማቸው። እነሆ ልክ እንደ አይሁዳውያን አሕዛብም ሲባረኩ አዩ። ጴጥሮስም፣ “እነኝህ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቀዋል። ታዲያ በውኃ እንዳይጠመቁ የሚከለክላቸው ነገር አለ?” ብሎ ጠየቀ።

- በኢየሱስ ስምም እንዲጠመቁ አዘዛቸው። ጴጥሮስንም ከእነርሱ ጋር አብሯቸው ለጥቂት ጊዜ እንዲቆይ ጠየቁት። አሁን እንደቀድሞው አጠራር ጴጥሮስ ያለው “ባልነፁ” ሰዎች ቤት ውስጥ ሳይሆን በክርስቲያን ወንድሞቹና እሕቶቹ ቤት ውስጥ ነው።

- ይህን የሰሙ አይሁዳውያን ወንድሞቹ እጅግ ተበሳጩ። ሆኖም ግን ጴጥሮስ ከመጀመሪያው አንስቶ ታሪኩን ነገራቸው። በተጨማሪም ከእርሱ ጋር አብረውት የሄዱ ስድስት አይሁዳውያንም ማረጋገጫ ሰጡ። ከዚያም መበሳጨታቸውን ትተው እግዚአብሔር በእርግጥ አሕዛብን እንደተቀበለ አውቀው እግዚአብሔርን አመሰገኑ።

*የቆርኔሌዎስ ታሪክ የሚገኘው በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 10፡ 23 – 48 ውስጥ ነው።*

http://gardenofpraise.com